# አፍሪቃ

በአውሮፓ - አሜሪካ የንግድ አደባባይ
ተሸጠን ተገዝተን በአረብ ባሪያ ፈንጋይ
በደም ግብር ትግል ከባርነት ወጥተን
ስብዕና የሌለው ነፃነት አግኝተን
የወርቅ ማዕድን የአልማዝና ኮባልት
ዩራኒየም መዳብ እምቅ ነዳጅ ዘይት
አመንጭዎች ሆነን ሸቀጥ የትርፍ ዕቃ
ሀብት የሞላን ድሆች ተገዥ ነን አፍሪቃ።

የነጭና ቢጫ ዘር የበላይነት
የአረቡን ዕቡይ ትዕቢትና ትምክህት
አንገት የሚያስደፉ ስልጣኔና ዕውቀት
የአህጉር ሃይል ሆነን እስካላስጨነቅናት
ዓለም አታወቀንም እኛ እንኳ ብናውቃት።

ነሃሴ 2003
አብርሃም በየነ

EthioLion.Com